የ29ኛዓመት ቁጥር 191፣
አሶሳ ህዳር 7/ 2015
ዓ.ም

# የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት

# ልሣነ-ህግ ጋዜጣ

ፖ.ሳ.ቁጥር፣293

ያንዱ ዋጋ‹-----

# LISAN HIG GAZETA

**Of the Council of the Benishangul Gumuze Regional State**

**በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት**

**ጠባቂነት የወጣ አዋጅ፣**

-----------------------------------------------------------------------------------------------------

## አዋጅ ቁጥ 191/2015 ዓ.ም

## የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት

## *የከተሞች አደረጃጀት፣ ሥልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 191/2015 ዓ.ም /ማሻሻያ/*

የተሻሻለዉ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት የከተሞች አደረጃጀት፣ ሥልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 141/2008 ዓ.ምን ማሻሻል አስፈሊጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ክልል ምክር ቤት በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ህገ-መንግስት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3 ተራ ቁጥር 1 በተሰጠዉ ሥልጣን መሰረት ታዉጇል፡፡

### አንቀጽ 1

### አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ “*የተሻሻለዉ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት የከተሞች አደረጃጀት፣ ሥልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 141/2008 ዓ.ም /ማሻሻያ/ አዋጅ ቁጥር 191/2015 ዓ.ም*” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## <u>አንቀጽ 2</u>

## <u>ማሻሻያ</u>

የተሻሻለዉ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት የከተሞች አደረጃጀት፣ ሥልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 141/2008 ዓ.ም እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

በአዋጁ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 15 ቀጥሎ በአዲስ ንዑስ አንቀጽ የተተካ እና ሌሎች የአዋጁ ይዘቶችም **"ቀጠና"** ከሚለዉ ወደ **"ቀበሌ"** ወደሚለዉ ተተክቷል፡፡

1. "አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 15 *"ቀበሌ"* ማለት ቀደም ሲል ለቀጠና የተሰጠዉ ስልጣንና ተግባራት እንዲሁም ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም የፈርጅ አንድና ሁለት የከተማ አስተዳደር ሶስተኛ ደረጃ የአስተዳደር እርከን ሲሆን ለፈርጅ ሦስት ደግሞ ሁለተኛ ደረጃ የአስተዳደር እርከን ነዉ ፡፡" በሚለዉ ተተክቷል፡፡
2. የተሻሻለዉ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት የከተሞች አደረጃጀት፣ ሥልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 141/2008 ዓ.ም አጠቃላይ ይዘት ዉስጥ **"ቀጠና"** የሚለዉ **"ቀበሌ"** በሚለዉ ተተክቷል

## <u>አንቀጽ 3</u>

## <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከፀደቀበት ከህዳር 7 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አሶሳ፣ ህዳር 7ቀን 2015 ዓ.ም

አሻደሊ ሀሰን አልአጀብ

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት

ፕሬዝዳንት